የሰ/መ/ቁጥር 219708

ሐምሌ 28 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመትአሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የሐረሪ ህዝብ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ዐ/ህግ

ተጠሪ፡- ኮ/ብል ዘይዳን አብራሂም } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 00236 ሕዳር 16 ቀን 2014ዓ/ም በሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 15ቀን 2012ዓ/ም በተፃፈ ክሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)(ሀ) እና 540 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ መጋቢት 15ቀን 2011ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 2፡00-4፡00 ሰዓት ባለዉ ጊዜ ዉስጥ በሐረሪ ከተማ ቀበሌ 03 ልዩ ስሙ አቦከር ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ዉስጥ ኮ/ብል እስክንድር መሀመድ የተባለ የግል ተበዳይ ላይ በያዘዉ ክላሽኮቭ መሳርያ ተኩሶ በግራ እግሩ ጉልበቱ ላይ በመምታቱ በማድረሱ የግድያ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ሲል ተከራክሯል፡፡ በዚህም መነሻነት የአመልካች 4 ምስክሮች ከተደመጡ በኋላ ተጠሪው የተከሰሰበትን የሕግ ድንጋጌ ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ሐ) በመቀየር መከላከል እንዲጀምር ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የተጠሪው መከላከያ ምስክሮች ከተደመጡ በኋላ ተጠሪው የግል ተበዳዩን ለመግደል ወይም ለመጉዳት አስቦ ድርጊቱን የፈፀመ መሆኑን አልተረጋገጠም በሚል በነፃ እንዲሰናበት

ተወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የይግባኝና የሰበር አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይት በማጣቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካቹ ጥር 10ቀን 2014ዓ/ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታው በጥቅሉ በተጠሪው እና በግል ተበዳይ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የግል ተበዳይን ለመጉዳት አስቦ ተኩሶ መምታቱ በተረጋገጠበትና ተጠሪውም በመከላከያ ማስረጃ ባላስተባበለበት ተከላክሏል በሚል በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው

ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪው በክላሽ ጠመንጃ ተኩሶ የግል ተበደይን እግሩ ቢመታም ወንጀል ለመፈፀም የሐሳብ ክፍል የለዉም ተብሎ ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት የመወሰኑን አግባብነት በዚህ ችሎት እንዲጣራ ታዞ ተጠሪም የመልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 20ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሱ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በመሆኑም ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ  ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን ተጠሪው በክላሽ ጠመንጃ ተኩሶ የግል ተበደይን እግሩ ቢመታም ወንጀል ለመፈፀም የሐሳብ ክፍል የለዉም ተብሎ በነፃ እንዲሰናበት በተሰጠው ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብተነት ተይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚቀጣው አስቀድሞ በወጣ ሕግ እንዳፈፅም ተከለከለውን ወይም እንዲፈፅመው በሕግ ግዴታ የተጣለበትን ድርጊት አስቦ ወይም በሚያስቀጣ ቸልተኝነት መፈፀሙ በማስረጃ በተረጋገጠ ጊዜ እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

በቀረበው ጉዳይ ተጠሪው የተከሰሰው የግል ተበዳይን ለመግደል አስቦ በያዘው ክልሽንኮቭ ጠመንጃ ተኩሱ የተበዳይን የግራ እግር ጉልበት የመታው በመሆኑ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡ ተጠሪው ድርጊቱን አልመፈፀምኩም ሲል ተከራክሯል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ተጠሪውን ጨምሮ ሌሎች የፖሊስ አባላት የስራ ሀላፊነታቸውን በመወጣት ላይ ሣሉ የያዟቸውን ሰዎች ለማስለቀቅ ከህዝብ ጋር ሆኖ ረብሻ ያስነሣውን የግል ተበዳይ አንተን ብሎ በጥይት ተኩሶ የመታው መሆኑን መስክረዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት መከላከያ ምስክሮች ደግሞ የእስረኞች ቤተሰቦች ስማስመለጥ ጥረት ሲያደርጉ በአካባቢው ከ200 ሰው በላይ መሰብሰቡን በፖሊስ ተጨማሪ ሐይል ተጠይቆ ተጠሪውን ጨምሮ ሌሎች የፖሊስ አባላት ደርሰው ተጠሪው የያዘውን መሣሪያ አቀብብሎ ጉዳዩን ስርዓት ለማስያዝ ስራውን ሲሰራ መሣሪያውን ለመቀማት ያሰቡ ሰዎች መሣሪውን ይዘው ሲታገሉ ጥይት መቃረቁን የግል ተበዳይ እግር ሣይታሰብ መመታቱን ተተሪውም በድንጋይ መፈንከቱን እስረኞችም ማምለጣቸውን ሌላም የፖሊስ አባል መጎዳቱን የግል ተበዳይ የተመታው በተጠሪው መሣሪያ በተተኮሰ ጥይት ወይም በሌላ ሰው በተኮሰው ጥይት እንደማይታወቅ መስክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤቱም አመልካች መሣሪያውን ያቀረባበለው ከተፈጠረው ረብሻ ራሱን ለመከላከል

እንደሆነና የግል ተበዳይ የተመታው መሣሪያው ባርቆ መሆኑን መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ተጠሪው አስቦ የወንጀል ድርጊቱን አለመፈፀሙን በማስረዳት የአመልካችን ማስረጃ አስተባብሏል ሲል በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል

በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ፀንቷል፡፡

በመሆኑም የአመልካች ምስክሮች ተጠሪው የግል ተበዳይን ሆን ብሎ ተኮሶ ጉልበቱን የመታው መሆኑን ቢያረጋጉጡም ድርጊቱ ሲፈፀም በአካባቢው ግርግር የነበረ መሆኑን፣ የተፈጠረው ግርግርም ተጠሪውና የስራ ባልደረቦቹ ሕግ የማስከበር ሃላፊታቸውን እንዳይወጡ ታስቦ መሆኑን፣ የተጠሪውን መሣሪያ ለመንጠቅ ያሰቡት ሰዎች ጋር በተፈጠረ ትግል መሣሪያው መባረቁ በዚህ ጊዜ በማን ጥይት እንደሆነ መለየት በማይቻልበት ሁኔታ የግል ተበዳይ እግር መመታቱን፣ ተጠሪውም በድንጋይ መፈንከቱ ሌላው ፖሊስም ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በመከላከያ ማስረጃ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሣኔ ቅጅ ያስገነዝባል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪው የአመልካችን ማስረጃ አስተባብሏል ሲል ወስኗል፡፡

ይህ የስር ፍርድ ቤት መደምደሚያ ከወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ሲመርመር በአመልካች ማስረጃ ላይ የተፈጠረው ጥርጣሬ ከምክንያተዊ ጥርጣሬ በላይ በመሆኑ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪውን በነፃ በማሰናበቱ የማስረጃ ምዘና መርህን የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀፅ 10 (1)(ሐ)(መ) በሚደነግጉት አኳኋን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀበት ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 00236 ሕዳር 16 ቀን 2014ዓ/ም የሰጠዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ